

# የሕዝባዊ ስብሰባ ማስታወቂያ

**ዋሽንግተን ሜትሮፖሊታን ኤሪያ ትራንዚት ኦቶሪቲ (የዋሽንግተን ከተማ አካባቢ የብዙሃን ትራንስፖርት ባለሥልጣን)**

**ርዕሰ ጉዳይ B14-01፡- የ2015 በጀት ዓመት የትራንስፖርት ክፍያ ተመኖች ማሻሻያ የውሳኔ ሃሳብ እና**

**ርዕሰ ጉዳይ B14-02፡- የ2015 በጀት ዓመት የካፒታል ማሻሻያ ፕሮግራም እና የፌደራል የ2014 የበጀት ዓመት የድጋፍ ማመልከቻዎች የውሳኔ ሃሳብ**

**ዓላማ**

**ከላይ በተጠቀሱት ሁለት ርዕሰ ጉዳዮች ላይ በዋሽንግተን ሜትሮፖሊታን ኤሪያ ትራንዚት ኦቶሪቲ (የዋሽንግተን ከተማ አካባቢ የብዙሃን ትራንስፖርት ባለሥልጣን) ስድስት ሕዝባዊያን ስብሰባዎች የሚካሄዱ መሆኑን ለማሳወቅ ይህ ማስታወቂያ ወጥቷል፤ ስብሰባዎቹም የሚካሄዱት እንደሚከተለው ነው፡-**

ስብሰባ ቁጥር 589
<u>ረቡዕ፣ ጃንዋሪ 29 ቀን 2014 ዓ.ም.</u>
Greenbelt Marriott
6400 Ivy Ln
Greenbelt, MD
ወደ ግሪንቤልት (Greenbelt) ጣቢያ ለመሄድ እና ከዚያ ለመመለስ ነጻ መጓጓዣ ይቀርባል

ስብሰባ ቁጥር 590
<u>ሐሙስ፣ ጃንዋሪ 30 ቀን 2014 ዓ.ም.</u>
Hilton Springfield
6550 Loisdale Rd
Springfield, VA
7፡30 pm በኋላ ወደ ፍራንኮኒያ-ስፕሪንግፊልድ (Franconia-Springfield) ጣቢያ ለመሄድ እና ከዚያ ለመመለስ ነጻ መጓጓዣ ይቀርባል

ስብሰባ ቁጥር 591
<u>ሰኞ፣ ፌብርዋሪ 3 ቀን 2014 ዓ.ም.</u>
Matthews Memorial Baptist Church
Fellowship Hall
2616 Martin Luther King Jr Ave, SE Washington, DC

ስብሰባ ቁጥር 592
<u>ማክሰኞ፣ ፌብርዋሪ 4 ቀን 2014 ዓ.ም.</u>
Montgomery County Executive Office Building Cafeteria
101 Monroe St
Rockville, MD
(መግቢያው በጀፈርሰን መንገድ (Jefferson St) ይገኛል)

ስብሰባ ቁጥር 593
<u>ረቡዕ፣ ፌብርዋሪ 5 ቀን 2014 ዓ.ም.</u>
Arlington Central Library
1015 N Quincy St
Arlington, VA

ስብሰባ ቁጥር 594
<u>ሐሙስ፣ ፌብርዋሪ 6 ቀን 2014 ዓ.ም.</u>
Metro Headquarters Building
600 5th St, NW
Washington, DC

**ለእያንዳንዱ የስብሰባ ስፍራ፡- የመረጃ መስጫ ክፍለ ጊዜ በ6 p.m. ይሆናል፡፡ ሕዝባዊ ስብሰባው በ6፡30 p.m. ይጀምራል፡፡**

**በእያንዳንዱ ተቋም የአስቸጋሪ የአየር ሁኔታ ፖሊሲ መሠረት እነዚህ የስብሰባ ቀናት ላይ ለውጥ ሊደረግ እንደሚችል በትህትና እናሳስባለን፡፡ እንዲህ ባለው መልኩ ስብሰባው ከተሰረዘ፣ ሜትሮ (Metro) ስለተለዋጭ የስብሰባ ቀን በ wmata.com አማካኝነት መረጃ ይሰጣል፡፡**

ሁሉም ሕዝባዊያን የስብሰባ ስፍራዎች ለዊልቼር (ለአካል ጉዳተኞች ወንበሮች) ምቹ ናቸው፡፡ ማንኛውም ሰው በሕዝባዊ ስብሰባዎቹ ላይ ለመሳተፍ ልዩ ድጋፍ፣ ለምሳሌ፡- የምልክት ቋንቋ አስተርጓሚ ወይም ተጨማሪ ግልጋሎት ካስፈለገው/ጋት፣ ወይም እነዚህን ጽሁፎች በሌላ ፎርም ማግኘት የሚፈልግ/የምትፈልግ ከሆነ፣ ሜትሮ (Metro) አስፈላጊ ዝግጅቶች ማድረግ እንዲችል በስልክ ቁጥር 202-962-2511 በመደወል ከዴኒስ ፔና (Danise Peña) ጋር መነጋገር ወይም በስልክ ቁጥር 202-962-2033 ለ TTY በመደወል በተቻለ ፍጥነት ማሳወቅ ይኖርበታል/ይኖርባታል፡፡ የቋንቋ ድጋፍ ለማግኘት ማለትም አስተርጓሚ እንዲመደብ ወይም በሌላ ቋንቋ መረጃ ለማግኘት እባክዎን ሕዝባዊ ስብሰባው ከሚካሄድበት ቀን ቢያንስ 48 ሰዓታት ቀደም ብለው በስልክ ቁጥር 202-962-2582 በመደወል ያሳውቁ፡፡

**ለተጨማሪ መረጃ የሚከተለውን ድረ-ገጽ ይጎብኙ፡-** www.wmata.com/hearings

metro

በ WMATA (ዋሽንግተን ሜትሮፖሊታን ኤሪያ ትራንዚት ኦቶሪቲ) ሥምምነት በክፍል 62 መሠረት፣ ሜትሮ (Metro) በዚህ ማሳወቂያ በተጠቀሱት ሥፍራዎች ስድስት ሕዝባዊ ስብሰባዎች ያካሂዳል፡፡ ሕዝባዊ ስብሰባዎቹን የተመለከቱ መረጃዎች በአካባቢ ቤተ-መጻሕፍት፣ በሜትሮባስ (Metrobus)፣ ሜትሮሬይል (Metrorail) እና በሜትሮ አክሰስ (MetroAccess) ተሽከርካሪዎች እንዲሁም በድረ-ገጽ www.wmata.com/hearings ይገኛሉ፡፡

**<u>ንግግር ለማድረግ ስለመመዝገብ</u> :–** ከእነዚህ ሁለት ርዕሰ ጉዳዮች በማናቸውም ላይ ሃሳብ መስጠት የሚፈልጉ ድርጅቶች እና ግለሰቦች ሁሉ ሃሳቦቻቸውን ለማቅረብ፣ የድጋፍ አስተያየቶች እንዲሁም አማራጭ ምክረ ሃሳቦች ለመስጠት ዕድል ይመቻችላቸዋል፡፡ የምሥክሮችን ዝርዝር ለማቅረብ፣ በእነዚህ ሕዝባዊያን ስብሰባዎች ላይ ንግግር ለማድረግ የሚሹ ግለሰቦች እና የድርጅቶች ወኪሎች ሥሞቻቸውን እና ከድርጅቶቹ ጋር ያላቸውን ግንኙነት (ግንኙነት ካላቸው) በኢ-ሜይል አድራሻ speak@wmata.com በጽሁፍ እንዲያሳውቁ እንጠይቃለን፡፡ በተጨማሪም ንግግር የማድረግ ጥያቄው ለዋሽንግተን ሜትሮፖሊታን ኤሪያ ትራንዚት ኦቶሪቲ (የዋሽንግተን ከተማ አካባቢ የብዙሃን ትራንስፖርት ባለሥልጣን) ጸሃፊ መሥሪያ ቤት ከዚህ በሚከተለው የፖስታ አድራሻ ሊቀርብ ይችላል፡- 600 Fifth Street, NW, Washington, D.C. 20001:: በአማራጭነትም ይህንን መረጃ በሚከተለው የፋክስ ቁጥር መላክ ይችላሉ፡- 202-962-1133፡፡ እባክዎን ለእያንዳንዱ ደብዳቤ የአንድ ተናጋሪን ሥም ብቻ እንዲያቀርቡ በአክብሮት እንጠይቃለን፡፡ የግለሰብ ተናጋሪዎች ዝርዝር ተቀባይነት አይኖረውም፡፡ እንዲህ ያለው መረጃ በዋሽንግተን ሜትሮፖሊታን ኤሪያ ትራንዚት ኦቶሪቲ ፐብሊክ አክሰስ ቱ ሪከርድስ ፖሊሲ (PARP) መሠረት ለሕዝብ ይፋ ሊደረግ እንደሚችል እንዲያውቁ በአክብሮት እናሳስባለን፡፡ የ PARP (ፐብሊክ አክሰስ ቱ ሪከርድስ ፖሊሲ) ይዘት በዋሽንግተን ሜትሮፖሊታን ኤሪያ ትራንዚት ኦቶሪቲ ድረ-ገጽ wmata.com/about_metro/public_rr.cfm "Legal Affairs" በሚለው ርዕስ ስር ይገኛል፡፡ መጀመሪያ የመንግሥት ባለስልጣናት ንግግር ያደርጋሉ፤ እያንዳንዳቸውም ሃሳቦቻቸውን ለማቅረብ አምስት አምስት ደቂቃዎች ይኖሯቸዋል፡፡ ሌሎች ተናጋሪዎች ሁሉ እያንዳንዳቸው ሦስት ሦስት ደቂቃዎች ይመደቡላቸዋል፡፡ ተናጋሪዎች በአንዱም ሆነ በሁለቱም ርዕሰ ጉዳይ/ጉዳዮች ላይ ንግግር ማድረጋቸው ከግምት ውስጥ ሳይገባ እነዚህ የጊዜ ገደቦች ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡ አንዱ ተናጋሪ የንግግር ጊዜውን ለሌላ ተናጋሪ አሳልፎ መስጠት አይፈቀድለትም፡፡

**<u>ሃሳብን በጽሁፍ ስለማቅረብ</u> ፡-** በጽሁፍ የተዘጋጁ ሃሳቦች ወይም መግለጫዎች እና ማስረጃዎች በጸሃፊው መሥሪያ ቤት እስከ ማክሰኞ፣ ፌብርዋሪ 11 ቀን 2014 ዓ.ም. በ5፡00 p.m. መድረስ አለባቸው፤ እነርሱም በሚከተለው የኢ-ሜይል አድራሻ ሊላኩ ይችላሉ፡- writtentestimony@wmata.com፡፡ በተጨማሪም ለዋሽንግተን ሜትሮፖሊታን ኤሪያ ትራንዚት ኦቶሪቲ (የዋሽንግተን ከተማ አካባቢ የብዙሃን ትራንስፖርት ባለሥልጣን) ጸሃፊ መሥሪያ ቤት ከዚህ በሚከተለው የፖስታ አድራሻ ሊላኩ ይችላሉ፡- 600 Fifth Street, NW, Washington, D.C. 20001:: በአማራጭነትም ጽሁፎቹን ከዚህ በሚከተለው የፋክስ ቁጥር መላክ ይቻላል፡-202-962-1133:: እባክዎን ጽሁፎችዎን በሚያቀርቡ ጊዜ አግባብነት ያለውን የርዕሰ ጉዳይ ቁጥር ይጥቀሱ (B14-01 እና/ወይም B14-02)፡፡ በጽሁፍ በተዘጋጀው ሃሳብ ወይም መግለጫ ላይ የጠቀሷቸው ማናቸውም ግላዊ መረጃዎች፣ ለምሳሌ፡- ሥም፣ ኢ-ሜይል አድራሻ፣ አድራሻ ወይም ስልክ ቁጥር ከላይ በተገለጸው ድረ-ገጽ ውስጥ በተካተተው የዋሽንግተን ሜትሮፖሊታን ኤሪያ ትራንዚት ኦቶሪቲ፣ ፐብሊክ አክሰስ ቱ ሪከርድስ (የመረጃ ለሕዝብ ተደራሽነት) ፖሊሲ መሠረት ለሕዝብ ይፋ ሊደረጉ እንደሚችሉ እንዲገነዘቡ በአክብሮት እናሳስባለን፡፡

**<u>የዳሰሳ ጥናት</u>፡-** በተጨማሪም፣ ስለሜትሮ (Metro) በጀት እና የትራንስፖርት ክፍያዎች የዳሰሳ ጥናት ላይ መሳተፍ ከፈለጉ ከዚህ የሚከተለውን ድረ-ገጽ ይጎብኙ፡- wmata.com/budgetsurvey፡፡ ጥናቱ ከጃንዋሪ 2 ቀን 2014 ከ5፡00 p.m. ጀምሮ ክፍት ሆኖ በመቆየት በፌብርዋሪ 11 በ5፡00 p.m. ይዘጋል፡፡ ስለሜትሮ (Metro) የ2015 የበጀት ዓመት ሪቂቅ በጀት እና የትራንስፖርት ክፍያዎች እንዲሁም ስለ ስነሕዝብ ጉዳዮች ለተዘጋጁ ጥያቄዎች ምላሾች እንዲሰጡ ይጠየቃሉ፡፡ ይህ አማራጭ በሕዝባዊ ስብሰባው ወቅት ንግግር ለማድረግ ወይም በጽሁፍ ሃሳብዎን ለማቅረብ ካሉዎት አማራጮች በተጨማሪነት የቀረበ ነው፡፡ የጥናቱ ውጤቶች በጽሁፍ ከተዘጋጁት መግለጫዎች እና ከሕዝባዊ ስብሰባዎች አስተያየቶች ጋር በአንድነት ለቦርዱ ይቀርባሉ፤ በዚህም መልኩ የሕዝባዊ ስብሰባው ይፋዊ ሪከርዶች አካል ተደርገው ይያዛሉ፡፡

**ለርዕስ ጉዳይ B14-01 የዋሽንግተን ሜትሮፖሊታን ኤሪያ ትራንዚት ኦቶሪቲ የውሳኔ ሃሳብ፡- የ2015 በጀት ዓመት የትራንስፖርት ክፍያ ማሻሻያዎች የውሳኔ ሃሳብ**

በውሳኔ ሃሳብነት የቀረበው የ2015 በጀት $3.0 ቢሊዮን ሲሆን፣ ይህም በጀት ለሜትሮ (Metro) ደንበኞች በይበልጥ ደሕንነቱ የተጠበቀና የተሻለ የትራንስፖርት አገልግሎት መስጠትን እና ተጨማሪ አገልግሎቶች ማበርከትን ያለመ ነው፤ ሞመንተም (Momentum) ስትራቴጂያዊ ዕቅድን በርካታ ቁልፍ ተግባራት ከግምት ውስጥ በማስገባትም ክልሉን ለመጪው ጊዜ ዝግጁ እንዲሆን የሚያደርግ ነው፡፡ ከዚህም ሌላ የቀረበው ረቂቅ በጀት የኤጀንሲውን የሦስት ዓመት የሥራ ዕቅድ የሚደግፍ ሲሆን፣ የዕቅዱ መነሻ ደሕንነት ነው፤ በዚህ ዓመት ደግሞ ለደንበኞች የዕለት ተዕለት ግልጋሎት ልዩ ትኩረት የሚሰጥ ነው፡፡ ከጠቅላላው ረቂቅ በጀት መካከል $1.76 ቢሊዮን የሚሆነው በመላው ዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ (District of Columbia)፣ ሜሪላንድ (Maryland) እና ቨርጂኒያ (Virginia) ጥራት ያለው የሜትሮሬይል፣ ሜትሮባስ እና ሜትሮ አክሰስ አገልግሎቶችን ለመስጠት በሥራ ማስኪያጃ ወጪነት የሚውል ነው፡፡

በ2015 የበጀት ዓመት፣ ሲልቨር ላይን (Silver Line) በመባል ለሚታወቀው ከላርጎ፣ ሜሪላንድ (Largo, MD) እስከ ሮስተን፣ ቨርጂኒያ (Reston, VA) የሚዘልቅ ለሜትሮ የአገልግሎት መስመር የመጀመሪያው ሙሉ የበጀት ዓመት ነው፡፡ አዲሱ መስመር የሜትሮሬይል አገልግሎትን በቨርጂኒያ በ11.4 ማይል እና በአምስት ተጨማሪ ጣቢያዎች የሚያስፋፋ ነው፡፡

ከ 2015 የበጀት ዓመት ጀምሮ፣ ሜትሮ (Metro) ለመጀመሪያ ጊዜ 7000 ተያያዥ ተሽከርካሪ ያለውን መጓጓዣ ለአገልግሎት ያውላል፡፡ እነዚህ መጓጓዣ ተሽከርካሪዎች ልዩ ልዩ የደሕነት መጠበቂያዎችን ያካተቱ ከመሆኑም ሌላ የንድፍ ገጽታዎቻቸውም የደንበኞችን ምርጫዎች ከግምት ውስጥ ያስገቡ ናቸው፣ ለምሳሌ፡- ኤሌክትሮኒክ ጣቢያ እና የመዳረሻ ማሳያዎች ይካተታሉ፤ መተላለፊያዎቹ በይበልጥ ሰፋ ያሉ እና መቀመጫዎቹም የተሻሻሉ ናቸው፤ ለአካል ጉዳተኞች መንቀሳቀሻ ወንበሮች በቂ ስፍራ አለ፤ ማስታወቂያዎች በይበልጥ እንዲሰሙ ወይም እንዲደርሱ የሚያደርግ የተሻለ የመልዕክት ማስተላላፊያ ዘዴም አላቸው፡፡

ሜትሮ (Metro) ይህንን የብዙሃን የትራንስፖርት ሥርዓት ደሕንነት ለማስጠበቅ ተጨማሪ የመዋዕለ ንዋይ ፈሰስ ያደርጋል፣ ለመጓጓዣ ጥበቃ እና ለሲልቨር ላይን ተጨማሪ የፖሊስ አባላት ያሰማራል፤ አዲስ ዲስትሪክት II ንዑስ-ጣቢያ እና የሥልጠና ተቋም እና አዲስ የደሕንነት ሥራዎች ቁጥጥር ማዕከል (Security Operations Control Center) ያቋቁማል፡፡

ሜትሮ (Metro) ለመጀመሪያ ጊዜ መላውን ኤጀንሲ የሚሸፍን የደንበኞች እንክብካቤ ፕሮግራም ይመሠርታል፤ ይህም ፕሮግራም ደንበኞች በአውቶብስ፣ በባቡር እና በሜትሮአክሰስ በመጓዝ ላይ ሳሉ የሚስተናገዱባቸውን ደረጃዎች እና ፖሊሲዎች በግልጽ የሚያስቀምጥ ይሆናል፡፡ ሜትሮ (Metro) የደንበኞች ተሳትፎ ዕቅዶችን እና የቅጥር ስትራቴጂዎችን ተግባራዊ ያደርጋል፤ በዚህም ሥር በኤጀንሲው ውስጥ ቁልፍ በሆኑ የሥራ መደቦች ላይ ሠራተኞችን ለመቅጠር እና አቅማቸውንም ለማጎልበት በሚያስችል መልኩ ለቀጣይ የመተካካት ዕቅድ ልዩ ትኩረት መስጠት ይካተታል፡፡

በዕቅድ የቀረበው የሥራ ማስኬጃ በጀት በደንበኞች የትራንስፖርት ክፍያ እና በተሽከርካሪ ማቆሚያ አገልግሎት (52 በመቶ)፣ በክፍለ ግዛት እና በአካባቢ አስተዳደሮች መዋጮ (45 በመቶ) እንዲሁም በሌሎች የገቢ ምንጮች (3 በመቶ) የሚሸፈን ይሆናል፡፡ ሜትሮ (Metro) በቀጣዩ ዓመት የሚኖሩ አንዳንድ ጭማሪዎችን ለማካካስ የአስተዳደር ወጪዎችን ቀንሷል፣ ከፋይበር ኦፕቲክስ እና ከማስታወቂያ የሚያገኛቸውን ገቢዎች አሳድጓል፡፡

የቀረበው የሥራ ማስኬጃ በጀት ዕቅድ ከአካባቢ መስተዳደሮች የሚገኘውን ከሞላ ጎደል የ$44 ሚሊዮን ድጋፍ ያካተተ ነው፡፡ ከዚህም ባሻገር የሥራ ማስኬጃ ወጪው በ2015 የበጀት ዓመት የትራንስፖርት ክፍያ ጭማሪ እንደሚኖር ታሳቢ በማድረግ የተዘጋጀ ሲሆን፣ ከዚህም ጭማሪ በግምት $30 ሚሊዮን ተጨማሪ የተጣራ ገቢ ይገኛል፤ በዚህ ሥር በተጓዦች ቁጥር ዕድገት ምክንያት የሚገኝ ማናቸውም ተጨማሪ ገቢ ወይም ለሙሉ ዓመት ከሲልቨር ላይን አገልግሎት የሚገኘው ገቢ አልተካተቱም፡፡ ቦርዱ ይህንን ተጨማሪ ገቢ ለማስገኘት ልዩ ልዩ የክፍያ ማሻሻያዎችን ይዳስሳል፡፡

በዕቅድ የቀረቡት የትራንስፖርት ክፍያ ማሻሻያ የውሳኔ ሃሳቦች ከላይ ከተገለጸውም በተጨማሪ የሜትሮባስ የክፍያ መዋቅርን ለማቃለል እና ለጉባዔ ተካፋዮች በቅናሽ ዋጋ የይለፍ ሰነድ በማዘጋጀት የሜትሮ አገልግሎቶች ከከተማ ውጪ ለሚጓዙ ተጓዦች በይበልጥ ሳቢ እንዲሆኑ ታስበው የተዘጋጁ ናቸው፡፡ የቅናሽ ዋጋ የይለፍ ሰነድ ለጉባዔ ተሳታፊዎች የትራንስፖርት ክፍያ አማራጭን የሚሰጥ ሲሆን፣ በ$10 ዕለታዊ ክፍያ ያለገደብ የሜትሮሬይል ጉዞ ማድረግ ይችላሉ፤ በጉባዔው ርዝማኔ ላይም ተመሥርቶ የበርካታ ቀናት (ለምሳሌ፡- የሦስት ቀናት ወይም የአራት ቀናት) አገልግሎት ማግኘት ይችላሉ፡፡ በተጨማሪም፣ ሜትሮ (Metro) ለፌዴክስፊልድ (FedExField) ዝግጅቶች ልዩ የተሽከርካሪ ማቆሚያ ክፍያ ቅናሽ የማድረግ ዕቅድ ያለው ሲሆን፣ ክፍያውን ከ$25 ወደ $15 ለመቀነስ ታስቧል፤ የቅናሹ ዓላማ የቦታ አጠቃቀምን ለማሻሻል እና ከሌሎች በስቴዲየሙ አቅራቢያ ከሚገኙ የተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራዎች ይልቅ ተወዳዳሪ የሆነ አገልግሎት ለመስጠት ነው፡፡

በተለይ ደግሞ ሜትሮ (Metro) በቀጣይ ገጾች እንደተገለጸው በተጨማሪ የትራንስፖርት አገልግሎት ክፍያ ገቢ መልክ የተመለከተውን $30 ሚሊዮን ለማግኘት ተከታታይ የክፍያ ተመን ለውጦችን በዕቅድ አቅርቧል፡፡ ***የታቀዱት ለውጦች በ2015 በጀት ዓመት ሊደረግ የሚችለውን <u>ከፍተኛ</u> የትራንስፖርት ተመን ጭማሪን የሚያንጸባርቁ ሲሆን፣ ቦርዱ ከከፍተኛ ይልቅ አነስተኛ ጭማሪዎችን ለማድረግ ሊወስን ይችላል፡፡*** ለምሳሌ፣ ከዚህ በታች የተመለከተው የሜትሮሬይል የአገልግሎት ክፍያ ዕቅድ የ4 በመቶ ጭማሪን ታሳቢ ያደረገ ሲሆን፣ ቦርዱ የ3 በመቶ ወይም ማናቸውም ከ4 በመቶ በታች የሆነ ጭማሪን ሊወስን ይችላል፡፡

## የትራንስፖርት እና ሌሎች ክፍያዎች (ተፈጻሚ ሊደረጉ የሚችሉ ከፍተኛ ለውጦች)

| የሜትሮሬይል የትራንስፖርት ክፍያዎች | | ወቅታዊ የትራንስፖርት/ሌሎች ክፍያዎች | የ2015 የበጀት ዓመት ዕቅድ የትራንስፖርት ክፍያ ተመን አማራጮች |
|---|---|---|---|
| **የትራፊክ ፍሰት የሚጨናነቅባቸው ሰዓታት ክፍያ**[1] | | | |
| 1 | ·የመሳፈሪያ ክፍያ (እስከ 3 ማይል) | $2.10 | **$2.20** |
| 2 | · ከ3 እስከ 6 ማይል የረጅም ርቀት ጉዞ | $0.316 | **$0.329** |
| 3 | · ከ6 ማይል በላይ የረጅም ርቀት ጉዞ | $0.280 | **$0.291** |
| 4 | · የትራፊክ ፍሰት የሚጨናነቅባቸው ሰዓታት ከፍተኛው ክፍያ | $5.75 | **$6.00** |
| 5 | · የእድሜ ባለጠጎች/የአካል ጉዳተኞች የትራፊክ ፍሰት የሚጨናነቅባቸው ሰዓታት ከፍተኛ ክፍያ እኩሌታ | $1.05 - $2.85 | **$1.10 - $3.00** |
| **መደበኛ የትራፊክ ፍሰት ሰዓታት ክፍያ**[2] | | | |
| 6 | · የመሳፈሪያ ክፍያ (እስከ 3 ማይል) | $1.70 | **$1.75** |
| 7 | · ከ3 እስከ 6 ማይል የረጅም ርቀት ጉዞ | $0.237 | **$0.247** |
| 8 | · ከ6 ማይል በላይ የረጅም ርቀት ጉዞ | $0.210 | **$0.218** |
| 9 | ·መደበኛ የትራፊክ ፍሰት ሰዓታት ከፍተኛው ክፍያ | $3.50 | **$3.65** |
| 10 | ·በመደበኛ የትራፊክ ፍሰት ሰዓታት እድሜ ባለጠጎች/የአካል ጉዳተኞች የሚከፍሉት ክፍያ የትራፊክ ፍሰት ሚጨናነቅባቸው ሰዓታት ክፍያ እኩሌታ ነው | $1.05 - $2.85 | **$1.10 - $3.00** |
| **ማግኔቲክ ፔፐር የክፍያ ካርዶች** | | | |
| 11 | ·SmarTrip® ውጪ የክፍያ ሱርቻርጅ[3] | $1.00 | **ለውጥ አልተደረገም** |
| 12 | እድሜ ባለጠጎች/የአካል ጉዳተኞች ከSmarTrip® ውጪ ሱርቻርጅ | $0.50 | **ለውጥ አልተደረገም** |
| **የባቡር ጉዞ የይለፍ ሰነዶች** | | | |
| 13 | · የአንድ ቀን ገደብ የሌለው የይለፍ ሰነድ | $14.00 | **$14.50** |
| 14 | · የአንድ ቀን የጉባዔ ተሳትፎ ይለፍ (ለበርካታ ተጓዦች ሽያጭ ብቻ)[4] | አግባብነት የለውም | **$10.00** |
| 15 | · የ7 ቀናት አጭር የባቡር ጉዞ | $35.00 | **$36.50** |
| 16 | · የ7 ቀናት የባቡር ጉዞ ፈጣን ይለፍ | $57.50 | **$59.75** |
| 17 | ·የ28 ቀናት የባቡር ጉዞ ፈጣን ይለፍ | $230.00 | **$239.00** |
| 18 | · SmarTrip® card በመጠቀም ከአውቶብስ ወደ ባቡር ለመሸጋገር | የ$0.50 ቅናሽ | **ለውጥ አልተደረገም** |
| 19 | · በዲስትሪክት ኦፍ ኮሉምቢያ ውስጥ የ30 ቀናት የ DC SmartStudent ይለፍ ካርድ እና DC One ካርድ | $32.00 | **$33.00** |
| 20 | · DC Student የክፍያ ካርዶች እና DC One ካርድ፣ በዲስትሪክት ኦፎ ኮሉምቢያ ውስጥ 10 የባቡር ጉዞዎች | $10.00 | **$10.40** |
| 21 | · በ MARC እና VRE TransitLink ካርድ [5] | $108.00 | **$112.00** |
| 22 | · በ MTA TransitLink ካርድ [5] | $166.00 | **$173.00** |

| የሜትሮባስ የትራንስፖርት ክፍያዎች | | ወቅታዊ የትራንስፖርት/ሌሎች ክፍያዎች | የ2015 የበጀት ዓመት የትራንስፖርት ክፍያ አማራጮች |
|---|---|---|---|
| **መደበኛ የትራንስፖርት ክፍያዎች** | | | |
| 23 | · ለከተማ ክልል/የተወሰነ ፎርማታ አውቶብስ SmarTrip® የመሳፈሪያ ክፍያ | $1.60 | **$1.85** |
| 24 | · የፈጣን አውቶብስ SmarTrip® የመሳፈሪያ ክፍያ | $3.65 | **$4.00** |
| 25 | · ለከተማ ክልል/የተወሰነ ፎርማታ አውቶብስ በጥሬ ገንዘብ የመሳፈሪያ ክፍያ | $1.80 | **$2.00** |
| 26 | · የፈጣን አውቶብስ በጥሬ ገንዘብ የመሳፈሪያ ክፍያ | $4.00 | **$4.50** |
| 27 | · ተለይተው ለታወቁ የአውሮፕላን ማረፊያ መንገዶች የጥሬ ገንዘብ/ SmarTrip® መሳፈሪያ ክፍያ | $6.00 | **$7.00** |

**የእድሜ ባለጠጋ/አካል ጉዳተኛ፡- የመደበኛ የትራንስፖርት ክፍያዎች እኩሌታ**

| | | | |
|---|---|---|---|
| 28 | ·ለከተማ ክልል/የተወሰነ ፌርማታ አውቶብስ SmarTrip® የመሳፈሪያ ክፍያ | $0.80 | **$0.90** |
| 29 | · የፈጣን አውቶብስ SmarTrip® የመሳፈሪያ ክፍያ | $1.80 | **$2.00** |
| 30 | · ለከተማ ክልል/የተወሰነ ፌርማታ አውቶብስ በጥሬ ገንዘብ የመሳፈሪያ ክፍያ | $0.90 | **$1.00** |
| 31 | · የፈጣን አውቶብስ በጥሬ ገንዘብ የመሳፈሪያ ክፍያ | $2.00 | **ለውጥ አልተደረገም** |
| 32 | · ተለይተው ለታወቁ የአውሮፕላን ማረፊያ መንገዶች የጥሬ ገንዘብ/ SmarTrip® መሳፈሪያ ክፍያ | $3.00 | **$3.50** |

**የአውቶብስ ሽግግር**

| | | | |
|---|---|---|---|
| 33 | ·SmarTrip® ካርድን በመጠቀም ከአውቶብስ ወደ አውቶብስ መሸጋገር | ይለያያል | **ለውጥ አልተደረገም** |
| 34 | ·SmarTrip® ካርድን በመጠቀም ከባቡር ወደ አውቶብስ መሸጋገር | የ$0.50 ቅናሽ | **ለውጥ አልተደረገም** |
| 35 | ·ሳምንታዊ/ወርሃዊ ይለፍን በመጠቀም ከMARC፣ VRE እና MTA ሽግግር ማድረግ | $0.00 | **ለውጥ አልተደረገም** |
| 36 | ·ከክልላዊ የአውቶብስ ትራንስፖርት አጋሮች መሸጋገር | ይለያያል | **ለውጥ አልተደረገም** |

**የአውቶብስ ይለፍ**

| | | | |
|---|---|---|---|
| 37 | · የ7 ቀናት ክልላዊ የአውቶብስ ይለፍ | $16.00 | **$18.50** |
| 38 | ·የ7 ቀናት ክልላዊ የዕድሜ ባለጠጎች/የአካል ጉዳተኞች ይለፍ | $8.00 | **$9.25** |

**ሌላ የትራንስፖርት ክፍያ ዘዴ**

| | | | |
|---|---|---|---|
| 39 | · ለድርጅቶች 10 ልዩ መገልገያዎችን ያካተተ ማዕቀፍ | $18.00 | **$20.00** |
| 40 | · DC የተማሪዎች መገልገያዎች፣ በእያንዳንዱ ማዕቀፍ 10 ጉዞዎች | $8.00 | **$9.25** |
| 41 | ·በ DC One ካርድ የተማሪዎች ይለፍ፣ 10 ጉዞዎች | $8.00 | **$9.25** |

**የሜትሮአክሰስ የትራንስፖርት ክፍያዎች**[6]

| | | | |
|---|---|---|---|
| 42 | · የሜትሮአክሰስ የትራንስፖርት ክፍያ (በADA 3/4ኛ ማይል የአገልግሎት ወሰን) | ይለያያል | **ይለያያል** |
| 43 | · ከፍተኛው የትራንስፖርት ክፍያ | $7.00 | **ለውጥ አልተደረገም** |

**የተሽከርካሪ ማቆሚያ ክፍያዎች**[7]

| | | | |
|---|---|---|---|
| 44 | · ዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ | $3.50 - $4.50 | **$3.75 - $4.75** |
| 45 | · ሞንትጎምሬ ካውንቲ (Montgomery County) | $4.25 - $5.00 | **$4.50 - $5.25** |
| 46 | · ፕሪንስ ጆርጅስ ካውንቲ (Prince George's County)[8] | $4.50 | **$5.25** |
| 47 | · ቨርጂኒያ (Virginia) | $4.75 | **$5.00** |
| 48 | · ወርሃዊ የተያዘ ተሽከርካሪ ማቆሚያ ክፍያ | $45.00 - $65.00 | **ለውጥ አልተደረገም** |
| 49 | · የተሽከርካሪ ማቆሚያ ቆጣሪ $1.00/60 ደቂቃዎች | $1.00 | **ለውጥ አልተደረገም** |
| 50 | · የኒው ካሮልተን (New Carrollton) ፕሪክስ ጆርጅስ የተሽከርካሪ ማቆሚያ | $85.00 | **ለውጥ አልተደረገም** |
| 51 | · የሜትሮ (Metro) ተጓዦች ላልሆኑ ሰዎች የተሽከርካሪ ማቆሚያ ክፍያዎች | $8.25 - $25.00 | **$8.25 - $15.00** |

**ሌሎች ክፍያዎች**

| | | | |
|---|---|---|---|
| 52 | · የብስክሌት መቆለፊያ ኪራይ | $120.00 (ዓመታዊ) | **ለውጥ አልተደረገም** |
| 53 | · ለጣቢያዎች ማሻሻያዎች የመግቢያ/መውጫ ሱርቻርጅ፣ ሁለት ጣቢያዎች በእያንዳንዱ የረጅም ጉዞ ክልል[9] | $0.05 | **ለውጥ አልተደረገም** |

[1] *የትራፊክ ፍሰት በሚጨናነቅባቸው ሰዓታት የትራንስፖርት ክፍያ ተመኖች ተፈጻሚነት የሚኖራቸው በሳምንቱ ቀናት ከአገልግሎት መክፈቻ እስከ 9:30am እና ከ3:00pm እስከ 7:00pm ሲሆን፣ በብሔራዊ በዓላት ቀናት ተፈጻሚነት የላቸውም፡፡ የትራፊክ ፍሰት በሚጨናነቅባቸው ሰዓታት የትራንስፖርት ክፍያ ተመኖች በዓርብ እና ቅዳሜ ምሽቶች ከእኩለ ሌሊት እስከ መዝጊያ ተፈጻሚነት አላቸው፡፡*

[2] *መደበኛ የትራፊክ ፍሰት ሰዓታት የትራንስፖርት ክፍያ ተመኖች በሳምንቱ ቀናት፣ በቅዳሜ እና እሁድ ቀናት እንዲሁም በሁሉም ብሔራዊ የበዓላት ቀናት ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡*

[3] *ከSmarTrip® ውጪ ላሉት ሱርቻርጅ የሚጠየቀው የትራፊክ ፍሰት በሚጨናነቅባቸው እና በመደበኛ ጊዜያት ከሚከፈለው የትራንስፖርት ክፍያ በተጨማሪነት ነው፡፡*

[4] *ለጉባዔ ተሳታፊዎች ገደብ የሌለው፣ የአንድ ቀን ጉዞ ይለፍ በቅናሽ ዋጋ የሚቀርበው በዋሽንግተን ሜትሮፖሊታን ኤሪያ ትራንዚት ኦቶሪቲ የብዛት ሽያጭ አሠራር አማካኝነት ብቻ ነው፡፡*

[5] *በMARC፣ VRE እና MTA ሜትሮ (Metro) በ TransitLink ካርዶች ያለው ድርሻ*

*[6] በፈጣን ጉዞ ላይ በመመሥረት የሜትሮአክሰስ የትራንስፖርት ክፍያ ተመን ተነጻጻሪ ከሆነው የSmarTrip® ቁርጥ የጉዞ መስመር የክፍያ ተመን ሁለት እጥፍ ነው፡፡*

*[7] የተሽከርካሪ ማቆሚያ ክፍያዎች የሜትሮ (Metro) ዋና ክፍያን እና አስተዳደሩ የሚጠይቀውን ሱርቻርጅ ያካትታሉ፡፡ በኒው ካሮልተን (New Carrollton) ፕሪንስ ጆርጅስ የተሽከርካሪ ማቆሚያ የ$70 ዋና ክፍያ እና የ$15 ሱርቻርጅ ድምር ነው፡፡*

*[8] በፕሪንስ ጆርጅስ ካውንቲ በሚገኙ መገልገያዎች በመነሻ የተሽከርካሪ ማቆሚያ ክፍያ ላይ የ $0.25 ጭማሪ እና የ$0.50 ሱርቻርጅ፡፡*

*[9] ሱርቻርጅ የሚከፈልባቸው የባቡር ጣቢያዎች በእያንዳንዱ የአስተዳደር ክልል የተመደቡ ሲሆኑ፣ ተፈጻሚነታቸውም በቦርዱ የማጽደቂያ ውሳኔ ሲሰጥ ይሆናል፡፡*

በሕዝባዊ ስብሰባው ወቅት በሜትሮባስ፣ ሜትሮሬይል፣ ሜትሮአክሰስ፣ በተሽከርካሪ ማቆሚያ እና ሌሎች ክፍያዎች ላይ አስተያየቶች እንዲሰጡ ይጠየቃል፡፡ በዕቅድ የቀረቡት የማናቸውም ለውጦች ተፈጻሚነት የሚጀምረው በጁላይ 1 ቀን 2014 ዓ.ም. ወይም አከባቢ ይሆናል፡፡ በዕቅድ የቀረበው የ2015 የበጀት ዓመት የሥራ ማስኬጃ እና የካፒታል በጀት ዝርዝር መረጃዎች ከዚህ በሚከተለው ድረ-ገጽ ሊገኙ ይችላሉ፡- wmata.com/budget

## በርዕሰ ጉዳይ B14-02 ሥር የዋሽንግተን ሜትሮፖሊታን ኤሪያ ትራንዚት ኦቶሪቲ የውሳኔ ሃሳብ፡- የ2015 በጀት ዓመት የካፒታል ማሻሻያ ፕሮግራም እና የፌደራል የ2014 የበጀት ዓመት ድጋፍ ማመልከቻዎች የውሳኔ ሃሳብ

የዋሽንግተን ሜትሮፖሊታን ኤሪያ ትራንዚት ኦቶሪቲ በኤጀንሲው በመካሄድ ላይ ላሉት የካፒታል የመዋዕለ ንዋይ ፈሰስ ድጋፍ ለማግኘት ሲባል በሙቪንግ ኤሄድ ፎር ፕሮግረስ ኢን ዘ 21ስት ሴንቸሪ አክት (MAP-21) እና በ2008 በወጣው ፓሴንጀር ሬይል ኢንቬስትመንት ኤንድ ኢምፕሩቭመንት አክት (PRIIA) በ2014 የፌደራል መንግሥት በጀት ዓመት የድጋፍ ጥያቄ ማመልከቻ የማቅረብ ሃሳብ አለው፡፡ እነዚህ ማመልከቻዎች በMAP-21 (P.L. 112-141) እና PRIIA (P.L. 110-432) ሥር የሚቀርቡ ናቸው፡፡

በወቅታዊው ድልድል መሠረት የዋሽንግተን ሜትሮፖሊታን ኤሪያ ትራንዚት ኦቶሪቲ በእነዚህ ሦሥት የ MAP-21 ፕሮግራሞች አማካኝነት የ$292.4 ሚሊዮን ድጋፍ እንደሚያገኝ ይገመታል፡፡ በአርበናይዝድ ኤሪያ (Urbanized Area) በክፍል 5307 እና በሃይ ዴንሲቲ ስቴትስ ፎርሙላ ፕሮግራምስ በክፍል 5340 መሠረት ዋሽንግተን ሜትሮፖሊታን ኤሪያ ትራንዚት ኦቶሪቲ በድምሩ $145,029,626 የመመደብ ዕቅድ አለው፡፡ ይህም ዕቅድ ታሳቢ የሚያደርገው የሚቀረበው ማመልከቻ ተቀባይነት አግኝቶ በክፍል 5307 ስር የ$131,588,924 እና በክፍል 5340 ስር ደግሞ የ$13,440,702 የገንዘብ ድጋፎች ሊገኙ ይችላሉ በሚል ነው፡፡ ከዚህም ባሻገር የዋሽንግተን ሜትሮፖሊታን ኤሪያ ትራንዚት ኦቶሪቲ በፊክስድ ጋይድዌይ ሞደርናይዜሽን (Fixed Guideway Modernization) /ስቴት ኦፍ ጉድ ሪፔይር (State of Good Repair-Rail) ፕሮግራም በክፍል 5337 ስር $134,801,848 እንዲሁም ለአውቶብስ የትራንስፖርት አገልግሎት ደግሞ በፊክስድ ጋይድዌይ ፕሮግራም በክፍል 5337 ስር ተጨማሪ የ3,015,411 የገንዘብ ድጋፍ ከፌደራል መንግሥት ለማግኘት ያመለክታል፡፡ ተጨማሪም፣ ዋሽንግተን ሜትሮፖሊታን ኤሪያ ትራንዚት ኦቶሪቲ በአውቶብስ/አውቶብስ ፋሲሊቲስ (Bus/Bus Facilities) ፕሮግራም በክፍል 5339 ስር የ$9,521,063 የፌደራል መንግሥት የገንዘብ ድጋፍ ለማግኘት ማመልከቻ ያቀርባል፡፡

ከዚህም ባሻገር የዋሽንግተን ሜትሮፖሊታን ኤሪያ ትራንዚት ኦቶሪቲ በ PRIIA ፕሮግራም አማካኝንት የ$157,845,900 የገንዘብ ድጋፍ እንደሚያገኝ ይገምታል፡፡ የዋሽንግተን ሜትሮፖሊታን ኤሪያ ትራንዚት ኦቶሪቲ ለእነዚህ የገንዘብ ድጋፎች በቀጣዩ ዓመት ለማመልከት ያቅዳል፡፡ ይህም ዕቅድ የተዘጋጀው ምንም ዓይነት የገንዘብ አቅርቦት ዕገዳ እንደማይኖር እና በ2013 የፌደራል መንግሥት የበጀት ዓመት ታግዶ የነበረው ገንዘብ ተመላሽ እንደሚደረግ ታሳቢ በማድረግ ነው፡፡

የዋሽንግተን ሜትሮፖሊታን ኤሪያ ትራንዚት ኦቶሪቲ የ2015 የበጀት ዓመት በዕቅድ የቀረቡት የፕሮጀክት ፕሮግራሞች በከፊል በፌደራል መንግሥት 2014 የበጀት ዓመት በMAP-21 እና የ PRIIA የገንዘብ አቅርቦቶች ይደገፋል፡፡ የዋሽንግተን ሜትሮፖሊታን ኤሪያ ትራንዚት ኦቶሪቲ በዕቅድ የቀረቡት የፕሮጀክት ፕሮግራሞች እና ለፌደራል መንግሥት የትራንስፖርት አስተዳደር የሚቀርቡት ማመልከቻዎች ከዚህ በታች ተብራርተዋል፡፡

የዋሽንግተን ሜትሮፖሊታን ኤሪያ ትራንዚት ኦቶሪቲ ማጠቃለያ የፕሮጀክት ፕሮግራሞችን ለናሽናል ካፒታል ሪጅን ትራንስፖርቴሽን ፕላኒንግ ቦርድ (National Capital Region Transportation Planning Board) ያቀርባል፤ ይህም በፌደራል መንግሥት 2015 – 2020 የበጀት ዓመታት ለዋሽንግተን ከተማ አካባቢ ትራንስፖርቴሽን ኢምፕሩቭመንት ፕሮግራም (TIP) በግብዓትነት እንዲያገለግል ነው፡፡

## የፌደራል መንግሥት 2015 የበጀት ዓመት የዋሽንግተን ሜትሮፖሊታን ኤሪያ ትራንዚት ኦቶሪቲ የካፒታል ማሻሻያ ፕሮግራም

የዋሽንግተን ሜትሮፖሊታን ኤሪያ ትራንዚት ኦቶሪቲ_ በዕቅድ የቀረበ የ2015 የካፒታል ማሻሻያ ፕሮግራም (CIP) በጀት $1,137.3 ሚሊዮን ሲሆን፣ ይህም ትኩረት የሚያደርገው በደሕንነት ማሻሻያዎች፣ በሜትሮ ሥርዓት መልሶ ግንባታ፣ በሥርዓት አቅም ዕድገት እንዲሁም በወቅታዊ የባቡር እና የአውቶብስ ትስስር ውጤታማነት መሻሻል ላይ ነው፡፡ ግምታዊ ወጪዎች ሊጨምሩ ወይም ሊቀንሱ የሚችሉ ሲሆን፣ የፕሮጀክት ወሰኖች ወጥ ሆነው መቆየት አለባቸው፡፡ የሜትሮ (Metro) ሥርዓት ከተገነባበት ጊዜ ጀምሮ ሜትሮ (Metro) ከፍተኛ የማስፋፊያ ፕሮግራም የካፒታል መዋዕለ ንዋይ ፈስስ በማድረግ ላይ ሲሆን፣ አብዛኛው ገንዘብ የሚውለው ለደሕንነት፣ መልሶ ለማቋቋም እና የሜትሮን መሠረተ ልማት፣ መሳሪያዎች፣ መገልገያዎች፣ ሥርዓቶች፣ የባቡር ፉርጎዎች፣ አውቶቡሶች እና የሜትሮ የአክሰስ ተሽከርካሪዎችን ለመተካት ነው፡፡

በዕቅድ የቀረበው ፕሮግራም በፌደራል መንግሥት፣ በክፍለ ግዛት እና በአካባቢ አስተዳደሮች እንዲሁም በሌሎች አካላት የገንዘብ አቅርቦት ይደረግለታል፡፡ በዕቅድ የቀረበው ፕሮግራም ከጠቅላላው የ$1,137.3 ሚሊዮን የገንዘብ አቅርቦት ፍላጎት ውስጥ $487.5 ሚሊዮን በፌደራል መንግሥት እንደሚሸፈን ታሳቢ ያደረገ ነው፡፡ ቀሪው የፕሮግራሙ ክፍል ደግሞ ከክፍለ ግዛት እና ከአካባቢ አስተዳደር ምንጮች በሚቀርብ $522.1 ሚሊዮን፣ $110.0 ሚሊዮን የረጅም ጊዜ ብድር እንዲሁም ከሌሎች ምንጮች በሚገኝ $17.7 ሚሊዮን ይከናወናል፡፡

የካፒታል የመዋዕለ ንዋይ ፈሰስ ወይም ካፒታል ኢንቬስትመንት ከዚህ የሚከተሉትን የፕሮጀክት ክፍሎች ያካተተ ይሆናል፡-

- ***ተሽከርካሪዎች/የተሽከርካሪ መለዋወጫዎች***፣ በዚህም ሥር፡- ባሶችን መተካት፣ የመጓጓዣዎችን ብዛት ማሳደግ እና መጠገን፣ የባቡር ፉርጎዎች የደሕንነት እና አስተማማኝነት ማጠናከር፣ የሜትሮ አክሰስ ተሽከርካሪዎችን መተካት፣ መለዋወጫ ዕቃዎች፣ እና መከላከያ ጥገና ይካተታሉ፤
- ***የባቡር አገልግሎት መሠረተ ልማት ጥገና***፣ በዚህም ሥር፡- የባቡር መስመር መልሶ ጥገና ይካተታሉ፤
- ***የጥገና ተቋማት***፣ በዚህም ሥር፡- የአውቶብስ ገራዥ ጥገና እና መተካት፣ እንዲሁም የባቡር ማቆሚያ ዕድሳት እና የአቅም ማሻሻያ እና የጥገና ስፍራ መልሶ ማቋቋም ሥራዎች ይካተታሉ፤
- ***ሥርዓቶች እና ቴክኖሎጂ***፣ በዚህም ሥር፡- የኃይል አቅርቦት ሥርዓት ማሻሻያ፣ የአሠራር ድጋፍ ሶፍትዌር፣ የሥራ ድጋፍ ሶፍትዌር እና መሳሪያዎች እንዲሁም የባቡር ክፍያ መሳሪያዎች ይካተታሉ፤
- ***የጉዞ መስመር እና መዋቅሮች***፣ በዚህም ሥር፡- የጉዞ መስመር ማሻሻያ ሥራዎች፣ የጣቢያ እና የመተላለፊያ ፍሳሽ ማስወገድ ይካተታሉ፤
- ***የተጓዦች መገልገያዎች***፣ በዚህም ሥር አሳንሰር እና የአሳንሰር መገልገያዎች፣ እና የጣቢያ ዕድሳት ይካተታሉ፤
- ***ሌሎች ማሻሻያዎች***፣ በዚህም ሥር የጣቢያ አቅም ማጎልበት ፕሮጀክት፣ የአውቶብስ ቀደምት መተላለፊያዎች፣ እንዲሁም የብስክሌት እና የእግር ተጓዦች መገልገያ ማሻሻያዎች ይካተታሉ፤
- ***የጥገኛ መሳሪያዎች***፣ በዚህም ሥር፡- የባቡር እና የአውቶብስ ጥገና እና የሥራ ማስኬጃ መሳሪያዎች ይካተታሉ፤
- ***ሌሎች መገልገያዎች***፣ በዚህም ሥር፡- የሥራ እና የጉዞ ጥበቃ የፖሊስ አባላት መገልገያዎች ይካተታሉ፤
- ***የፕሮጀክት ሥራ አመራር እና ድጋፍ***

ፕሮጀክቶቹ ተግባራዊ በሚደረጉባቸው ጊዜያት ለአካል ጉዳተኞች እና ለዕድሜ ባለጠጎች ልዩ ትኩረት ይሰጣል፡፡ ሁሉም ፕሮጀክቶች በዋሽንግተን ከተማ አካባቢ አጠቃላይ የመሬት አጠቃቀም እና የትራንስፖርት ዕቅድ አወጣጥ ደንቦችን የሚያከብሩ ይሆናሉ፡፡ በእነዚህ ፕሮጀክቶች ምክንያት በአካባቢ ላይ ሊደርስ ይችላል ተብሎ የሚታሰብ አሉታዊ ተጽዕኖ የለም፡፡

በፌደራል ትራንዚት አድሚኒስትሬሽን (FTA) ደንብ 49፣ CFR ክፍል 604 መሠረት፣ በእነዚህ ደንቦች በልዩ ሁኔታ እንደተፈቀደው የዋሽንግተን ሜትሮፖሊታን ኤሪያ ትራንስፖርትኦቶሪቲ ከፍተኛ ቁጥር ላላቸው ተጓዦች ከሚሰጠው የትራንስፖርት አገልግሎት ጋር ተያይዞ አገልግሎቶችን በንዑስ ውል ለሌሎች አካላት በማስተላለፍ ይሰራል፡፡ የዋሽንግተን ሜትሮፖሊታን ኤሪያ ትራንስፖርትኦቶሪቲ በዚህ መልኩ በንዑስ ውል የሚያስተላልፋቸው አገልግሎቶች ሁሉ ቀጥተኛም ሆነ ተዘዋዋሪ የሥራ ማስኬጃ ወጪዎቻቸውን በራሳቸው የሚሸፍኑ ሲሆን፣ አገልግሎቶቹም የሚሰጡት በመደበኛ ተመኖች ነው፡፡ አገልግሎቶች እና ክፍያዎች በዋሽንግተን ሜትሮፖሊታን ኤሪያ ትራንስፖርት ኦቶሪቲ የንዑስ ውል እና በልዩ ትራንዚት አገልግሎት ታሪፍ ቁጥር 17 ላይ ታትመዋል፤ በኖቬምበር 20 ቀን 2008 ዓ.ም. በቦርዱ በተላለፈው የማሻሻያ ውሳኔ 2008-56 መሠረት ተፈጻሚነቱ የሚጀምረው በማርች 1 ቀን 2008 ዓ.ም. ነው፡፡ ለሕዝብ ግምገማ ይውሉ ዘንድ የታሪፍ እና የአውቶብስ ንዑስ ውል ወጪ ድልድል ዕቅድ ቅጂዎች በዋሽንግተን ሜትሮፖሊታን ኤሪያ ትራንስፖርት ኤጀንሲ የአውቶብስ አገልግሎት መምሪያ ይገኛሉ፡፡

**<u>ለግምገማ ሊውል የሚችል የጽሁፍ ማጣቀሻ</u>**

በዕቅድ የቀረበው የዋሽንግተን ሜትሮፖሊታን ኤሪያ ትራንስፖርት የ2015 የበጀት ዓመት የካፒታል ማሻሻያ ፕሮግራም በዋሽንግተን ሜትሮፖሊታን ኤሪያ ትራንስፖርት የ2015 ረቂቅ በጀት ውስጥ ተካቷል፤ ይህም ከዚህ በሚከተለው ድረ-ገጽ ሊገኝ ይችላል፡- wmata.com/budget፡፡

የ2015 በጀት ዓመት በዕቅድ የቀረበ በጀት ይገመገም ዘንድ በፌብሮዋሪ 11 ቀን 2014 ዓ.ም. እስከ 5 p.m.፣ የበዓላት ቀናትን ሳይጨምር ከሰኞ እስከ ዓርብ ከ9 a.m. and 5 p.m. በዋሽንግተን ሜትሮፖሊታን ኤሪያ ትራንዚት ኦቶሪቲ፣ 600 Fifth Street, NW, Washington, D.C. 20001 ሊገኝ ይችላል፡፡

ይህ የሕዝባዊ ስብሰባ ይፋዊ ማሳወቂያ እና በፕሮግራሙ ፕሮጀክቶች ለሕዝብ ግምገማ እና አስተያየት የተመደበው ሰዓት በ MAP-21 የተቀመጠውን የሕዝብ ተሳትፎ መስፈርቶች ያሟላ ነው፡፡ በዕቅድ በቀረበው የ2015 የፌደራል በጀት ዓመት የፕሮጀክት ፕሮግራም በዋሽንግተን ሜትሮፖሊታን ኤሪያ የዳይሬክተሮች ቦርድ የማጽደቂያ ውሳኔ ከማሳለፉ በፊት ካልተሻሻለ በቀር የፕሮጀክቶች የመጨረሻ ፕሮግራም ይሆናል፡፡